# የግንቦት 7 ድምጽ

አንብበው
ያስነብቡ !
አባዝተው
ያሰራጩ !

የግንቦት 7 ቋፍትሕ፣የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ሳምንታዊ ልሳን፤

www.ginbot7.org

ቁጥር 9 ሓምሌ 10 2000 ዓ.ም


## የመለስን ግፈኛ አገዛዝ ማርከሻው ቀበቶን፣ መቀነትን፣ ትጥቅን ማጥበቅ ብቻ ነው::

ሰሞኑን የአገዛዙ የመገናኛ ብዙሃን አውታሮች፣ የአገዛዙ ባለስልጣናት፣ ከአገዛዙ ጋር ሽርክና ያላቸው ጋዜጦችና ድረ-ገች በሙሉ ዴሞክራሲ ሂደት መሆኑን፣ ግንባታው ግዜ የሚፈጅ መሆኑን፣ ይህ ሂደት ሰላማዊና ህጋዊ በሆነ መንገድ በሚደረግ ትግል ብቻ የሚሳካ መሆኑን ለማስረዳት ብዙ እየደከሙ ነው:: “ከእዚህም አልፈው ከተቃዋሚው መሃል ሰላማዊና ህጋዊ በሆነ መንገድ እንታገላለን፣ አገዛዙ ያወጣቸውን ህጎችና መመሪያዎች እናከብራለን፣ ተቀራርበን እንሰራለን” ለሚሉ ድርጅቶችና ግለሰቦች ውዳሴያቸውን እየቸሩ ነው::

በሌላ በኩል ግን እነዚሁ አካላት፣ "የእዚህ አገዛዝ ቁንጮዎች ሃገር ከሃዲዎች፣ ነፍሰ ገዳዮች፣ ዘረኛ ከፋፋዮች፣ አፋኞች ናቸው:: ያገራችን የዴሞክራሲ ግንባታ ሂደት የፈለገውን ያህል ግዜ ቢፈጅ፣ በስልጣን ላይ ያለው የመለስ አገዛዝ የእዚህ የዴሞክራሲ ግንባታ ሂደት አካል ሊሆን መሰረታዊ ባህርይው አይፈቅድለትም:: እንዲህ አይነቱ አገዛዝ፣ ዴሞክራሲ፣ ነጻነትና የህግ የበላይነት በሃገር ላይ በአንዳች ተአምር ቢሰፍን ከስልጣኔ እነቀላለሁ፣ በዘረፍኩት፣ በገድልኩትና ሃገር በሸጥኩባቸው ወንጀሎች በሙሉ እጠየቃለሁ የሚል ስጋት አለው:: ይህንን ተጫበጭ ስጋቱን በተማጽኖ፣ በምልጃ፣ በሽምግልና፣ በምህላ፣ በቃልኪዳን ብዛት የሚቀይር አይደለም::" የሚሉትን ቡድኖችና ግለሰቦች እያወገዙ ነው::

"ይህ የገዥዎች ቡድን እየማለ፣ ቃል ኪዳን እየገባ፣ እየተለማመጠ አዘናግቶ ማረድና ማሰር ልመዱ አድርጎ የመጣ ነው:: መለስ ዜናዊን የህዝብ ወገኖች በፈጸምከው ወንጀል አንጠይቅህም፣ የዘረፍከውን ሃብት አንቀማህም፣ ለዴሞክራሲ የሚሆን እድል ስጠንና አለም በቃኝ ሳይሆን፣ የባህር በር ባሳጣሃት ሀገርህ፣ ለሱዳን መሬቷን ቆርሰህ ገጸ በረከት አድርገህ ባስረከብክባት ሃገርህ፣ በዘረፋ በገነባኸው ቪላ፣ ወንድሞቿቸውን ካሳረድክባቸው ወጣቶች መሃል በተመለመሉ ጠባቂዎች ተከበህ የቀረህን እድሜህን በሰላምና በቅንጦት ትኖራለህ ቢሉት ምላሹ ፋራ መሰልኳችሁ እንዴ የሚል እንደሚሆን የታወቀ ነው:: መለስ ዜናዊ እንዲህ አይነቱ የእርቅና የይቅርታ መንፈስ፣ በጎ ከሆነ “ለወገንና ለሃገር ከሚያስብ” ህሊና የሚፈልቅ አድርጎ የሚያይ አእምሮ የለውም:: ወታደራዊና የስለላ አቅሙን በመፍራት፣ በእርቅ ስም ከስልጣን አውርደው ሊሰቅሉት የሚፈልጉ ብልጣብልጦች ዘዴ አደርጎ ይመለከተዋል:: አምባገነኖች ሁሌም እንደሚያደርጉት መለስም ብዙ በተለመነ ቁጥር ንቀቱ እየጨመረ በእብሪቱ እያበጠበ የሚሄድ እንጂ ወደ ብትህውትና የሚመለስ መንፈስ የለውም:: የቆየና የቅርብ ታሪኩ የሚያሳየው ይህንኑ ነው:: በመሆኑም እንዲህ አይነቱ አምባገነናዊ አገዘዛ ለዴሞክራሲያዊ ስርአት መፈጠር ህዝብ በሚያደርገው ጥረት ፊት የቆመ ደንቃራ ነው" ብለው የሚከራከሩ ወገኖች በመለስ አገዛዝ ባለሚሎች ዱልዱም ብእር እየተወቀጡ ናቸው::

"እንዲህ አይነቱ አገዛዝ በበላይነት በሚቆጣጠረው መንግስታዊ ስርአት ውስጥ፣ ህግን፣ የአገዛዙ ባለስልጣናትን ህሊና፣ ሰብአዊ እሴቶችና ሌሎችንም ታሳቢዎች ግምት ውስጥ ያስገባ ህጋዊና ሰላማዊ ትግል ሊኖር አይችልም:: ምክንያቱም ገዥዎቹ የራሳቸውን ህግ እንኳን አያከብሩም:: ሰብአዊ ህሊና፣ ሃገራዊ ተቆርቋሪነት የላቸውም:: የሚያዋጣው ይህንን በእብሪት፣ በግፍና በንቀት የታጀለን አገዛዝ፣ መነሻና መድረሻውን ጠንቅቆ ባወቀ ራእይ በሚመራ፣ ሁሉንም አይነት የትግል ስልት በሚጠቀምና ሁሉንም ለዴሞክራሲና ለአንድነት የሚታገሉ ሃይሎችን በማስተባበር ታግሎ ከምድራችን መንቀል ነው::" በሚሉ ድርጅቶችንና ግለሰቦች ላይ የወያኔ አገዛዝ ወኪሎች ውግዘቱን፣ ማስፈራራቱን፣ ማንጓጠጡን ተያይዘውታል::

ወደ ገጽ 3 ዞሯል

## “በኢትዮጵያ ረሀቡና የኑሮ ውድነቱ እየተባባሰ ነው።"

"ማጅራት ገትርና ተቅማጥ በስፋት ተከስቷል" (ሴቭ ዘ ችልድረን)

“በቀን አንድ ጊዜ ብቻ እንበላለን” (የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች)

በኢትዮጵያ ሰብዓዊ ዕርዳታ እየተሰጠ ቢሆንም፤ ረሀቡና የኑሮ ውድነቱ እየከፋና እየተባባሰ መምጣቱ ተገለፀ።

በተለይ በአማራ፣ በደቡብ፣ በኦሮሚያና በሶማሌ ክልሎች ረሀቡ እጅግ አሳሳቢ ደረጃ ላይ መድረሱን የገለፀው ሴቭ ዘ ችልድረን ዩኬ፤የ እህል ዋጋም እስከ ሶስት እጥፍ ድረስ ማሻቀቡን አመልክቷል።

ወደገጽ2 ዞሯል

## የመለስ አገዛዝ ጸረ ኢትዮጵያዊነት መገለጫው ብዙ ነው::

**መልካም ልደት ቴዲ!!!**

« እኔ የማምነው ይህን ሁሉ ሰው በሚያይ እግዚያብሔር ነው። ግን አንድ ነገር መናገር እፈልጋለሁ። እኔ አንድም ሰው አልገደልኩም ሰውም አልገጨሁም። ነገር ግን በማላውቀው ነገር ሰብዓዊ መብቴ ተገፍፎ ቅማል እየበላኝ ሦስት ወር ታስሬያለሁ።

ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## ኢህአዴግ የዘረፈው ብር እየተድበሰበሰ ነው::

“ባንክ መዝረፍ የተካኑበት ነው” ( የአዲስ አበባ ነዋሪዎች)

“ የኦዲት ሪፖርቱ የኢትዩጵያን ስም የሚያጠፋ ነው::” (ሽፈራው ጃርሶ)

የፌዴራል ምክትል ዋና ኦዲተሩ አቶ አሰፋ ደስታ፤ ኢህአዴግ ራሱ ካወጣው መመሪያና ህግ ውጭ 3 ቢሊዮን 295 ሚሊዮን 400 ሺህ ብር በብድር መልክ ከባንክ መውሰዱን ባጋለጡ ማግስት፣ አቶ መለስ ያቋቋሙት አጣሪ ኮሚቴ፤ የኦዲት ሪፖርቱን ውድቅ አድርጎ ሌላ ሪፖርት በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዲያቀርብ የተላለፈለትን ትዕዛዛ አዘል ምክር ለማስፈፀም ደፋ ቀና እያለ መሆኑን ምንጮቻችን ገለፁ።

ወደ ገጽ 2 ዞሯል

# ርእሰ አንቀጽ

## የአሜሪካ ኤምባሲ ዳግም ሲሳሳት - «ምርጫ ቦርድን ፍትሃዊ ነው በሉ ፤ በሚቀጥለው ምርጫ የምትሳተፉ መሆኑን ካሁኑ አረጋግጡ»

ሰሞኑን የአሜሪካው አምባሳደርና ባልደረቦቻቸው የተቀናቃኝ ፓርቲ መሪ ዎችን እየጠሩ «ምርጫ ቦርድን ፍትሃዊ ነው ብላችሁ ተቀበሉ ፤ በሚቀጥለው ምርጫም እንደምትሳተፉ ቃል ግቡ» እያሉ አሻንጉሊት መንግስታቸውን ከገባበት መቀመቅ ለማዳን እየተራወጡ ነው:: አንድን አፋኝ አጎንባሽ የሆነ አምባገነን በሥልጣን ለማቆየት የአሜሪካ ኤምባሲ ምን ያህል መሄድ እንዳለበት የገባው አይመስልም ::

የአሜሪካ የውጪ ፖሊሲ «በብሄራዊ ጥቅም» ላይ የተገነባ መሆኑን ባለስልጣናቱ ደጋግመው ሲናገሩ ይደመጣል :: ሆኖም የአሜሪካ የደህንነት/ፀጥታ ፍላጎትና ጥቅም በምን መንገድ ከኢትዮጵያ የዴሞክራሲ ጥማት ጋር እንደሚቃረን ሊገባን አልቻለም :: ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ መገንባት ብትችል የአሜሪካ ብሄራዊ ጥቅም ይበለፅጋል እንጂ ይናዳል ብለን አናምንም:: ይልቁንስ የነፃነት ጎህ በኢትዮጵያ አድማስ መቅደዱ ሳይቀር ፤ አሜሪካ የአምባገነኖች ስንቅ አቀባይ፤ የህዝብ ተስፋ ቀባሪ፤ የሠላማዊ ሽግግር ፀር ሆና መታየቷ፤ መልኩዋን ያጠላዋል ብለን እንፈራለን ::

አምባሳደር ያማሞቶ ከሶስት አመታት በፊት ከአሜሪካ ኮንግረስ ፊት በመሃላ በሰጡት ቃል «ችግሩ ምርጫ ቦርድ አቅሙ ደካማ መሆኑ ነው» ማለታቸው ያሳዘነን መሆኑን እያወቁ፤ አሁን ደግሞ በ2002 ለሚካሄደው ሃገራዊ ምርጫ አስፈላጊ የሆኑ የነፃ ተቋማት ምሥረታ ጥያቄ አንገብጋቢ ቅድመ ሁኔታ መሆኑ ያገጠጠ ሃቅ ሆኖ ሳለ፤ ምርጫው ድጋሚ እንዲጭበረበርና፤ ወያኔ ያለምንም ተቀናቃኝ የስልጣን ዘመኑ እንዲራዘም ለማድረግ ያለመ ግፊት ማድረጋቸው የአሜሪካ ቀደምት አባቶች የነበራቸውን ህልም የሚፃረር ሆኖ አግኝተነዋል::

አንድ ህዝብ በጊዜያዊ የኢኮኖሚ ችግሩ የተነሳ ዕርዳታ የሚያስፈልገው ቢሆንም፤ የፖለቲካ ተፅእኖም ሊደረግበት ይገባል ማለት አይደለም :: የህዝብ ወገን የሆኑ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ወደኤምባሲ እየጠሩ ስለሚመሩበት ታክቲክና ስትራቴጂ መመሪያ መስጠት ከአሜሪካ የሰብአዊ ዕርዳታ መርሆና ፖሊሲ ጋርም የሚጣጣም ነው ብለን አናምንም:: በሃገራችን የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ መግባት እንዳይሆንም አንፈራለን:: አሜሪካ የተመሠረተችበት «በህግ የተደነገገ ነፃነት» (Ordered Liberty or Liberty Under the Law) ንቅናቄያችን የሚያምንበት መርሆ ነው:: ሆኖም ራሱ ላወጣው ህገ-መንግስት ራሱን ተገዢ ማድረግ ላልቻለ ዕ ብሪተኛ ሥርአት የአሜሪካ ኤምባሲ ከሚሰጠው ድጋፍ አልፎ፤ ተ ቀናቃኞችን የአምባገነኑ ተባባሪ እንዲሆኑ የሚያደረገው ተፅዕኖ አጅግ ያሳዘነን መሆኑን መግለፅ እንወዳለን:: በተለምዶ ከሚታወቀው የዲፕሎማሲ ሃላፊነት ክልል ውጪም እንዳይሆን ስጋታችን ከፍ ያለ ነው :: «የግንቦት7 ንቅናቄ» ከምርጫ 97 የተማረው መሪር ሃቅ ፤ ምርጫ ቦርድን የመሠሉ ተቋሞች ገለልተኛ ሳይሆኑ፤ ነፃ የሚዲያ ሥርጭት በሌለበት ሁኔታ፤ አምባገነንነትን "በምርጫ ማጽደቅ" እንጂ መቀየር አለመቻሉን ነው:: የአሜሪካ ኤምባሲም ይህ ሃቅ ይሰወረዋል ብለን አናስብም:: የኢትዮጵያን ህዝብ ማገዝና መርዳት ከፈለገም ፤ እነዚህ ነፃ ተቋማት እንዲፈጠሩ በአገዛዙ ላይ ተፅኖ ማድረግ እንጂ ፤ ዴሞክራሲንና ዕርዳታን ማቆላለፍ እንጂ፤ በመብት ዕጦትና ረሃብ የተቸገ ረን ህዝብ «ከመለስ የተሻለ አገዛዝ አይመጥንህም» በሚመስል ንቀት የነፃነት ጥማቱን ማጨናገፍ ሊሆን አይገባውም::

ከገጽ አንድ የዞረ፤ **በኢትዮጵያ ረሀቡና የኑሮ**

ይህ በእንዲህ እንዳለ፤ ከምግብ እህል ችግሩ ጋር በተያያዘ በቀን አንድ ጊዜ ብቻ እየበሉ ህይወታቸውን ለማቆየት መገደዳቸውን የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ተናገሩ።

የአዲስ አበባ፣ የአዋሳና የጅማ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ሰሞኑን እንደገለፁት፤ ከኑሮ ውድነቱ ጋር በተያያዘ በዩኒቨርሲቲያቸው የነበረው የወትሮ የምግብ አቅርቦት ሙሉ በሙሉ ተቀይሯል።

ከሳምንት ላላነሰ ጊዜ በተከታታይ ያለማቋረጥ የጓንለ ሩዝ እንደሚቀርብላቸው የተናገሩት ተማሪዎቹ፣ ሁሉም፤ ወትሮ በማያውቁት ከባድ የጨጓራ ህመም እየተሰቃዩ መሆናቸውን በሀኪም በማረጋገጣቸው፤ ህይወታቸውን ለማቆየት ያህል በቀን አንድ ጊዜ ብቻ ለመቀመስ መገደዳቸውን ገልጸዋል።

ስለ ጉዳዩ የተጠየቁት የየዩኒቨርሲቲዎቹ አስተዳደሮች፤ ችግሩ ከእነሱ አቅም በላይ እንደሆነና በዩኒቨርሲቲዎቹ ወቅታዊ አቅም ሊፈታ እንደማይችል ተናግረዋል።

ደፋሩ አዲሱ ለገሰ "የረሀቡን ወሬ እያባባሱት ያለው፤ ይህንን አስታከው በኢትዮጵያ ህዝብ ስም እየለመኑ ኪሳቸውን መሙላት የሚፈልጉ ግብረ-ሰናይ ድርጅቶች ናቸው፤ ችግሩ ከኛ ቁጥጥር እንደማይወጣ ላረጋግጥላችሁ እፈልጋለሁ" ብሎ በአደባባይ መናገሩ ይታወሳል።

አርብቶ አደሮች በሚኖሩባቸው የሶማሌ ዞኖች የውሀ ቢርካዎች ደርቀዋል፣ የግጦሽ ሳር ጠፍቷል፤ በዚህም ሳቢያ ከብቶች የሚበሉት አጥተው እየሞቱ ነው’ ብለዋል-የድርጅቱ ተወካይ።

ከጊዜ ወደ ጊዜ ሁኔታው እየተባባሰ እንጅ እየተሻሻለ ሊመጣ አልቻለም ያሉት የሴቭ ዘ ችልድረን ተወካይ፤ ድርቁ በከፋባቸው አካባቢዎች የማጅራት ገትር፣የተቅማጥና የኩፍኝ በሽታዎች በስፋት መከሰቱ ሁኔታውን እጅግ አሳሳቢ አድርጎታል ብለዋል።

ከገጽ 1 የዞረ፤ **ኢ.ህአዴግ የዘረፈው ብር**

ጉዳዩን በቅርበት እየተከታተሉ ያሉ ታማኝ ምንጮቻችን ለዝግጅት ክፍላችን ባደረሱን መረጃ መሰረት፤ በገለልተኛነት ስም አቶ መለስ ያቀረቧቸው አምስት የአጣሪ ኮሚቴ አባሎች፤ ቀንደኛ የኢ.ህአዴግ ደጋፊዎች በመሆናቸው፤ በኢ.ህአዴግ በኩል ስህተት እንዳልተፈፀመ የሚያሳይ ሪፖርት በፍጥነት ሰርተው ይፋ በማድረግ ገዥውን መንግስት በተለይ ከዓለም ባንክ ወቀሳ የሚታደግ ሪፖርት ሰርተው ያቀርባሉ ተብሎ ይጠበቃል።

ወደ ገጽ 4 ዞሯል

**አዘጋጆች**
ፋሲል የኔአለምና እና ደረጀ ሃ/ወልድ የቀድሞ
የአዲስ ዜና እና የነጻነት ጋዜጣ አዘጋጆች

**የፖስታ ሳጥን ቁጥር**
POBox: 4916
2003EX Haarlem
The Netherlands

**የግንቦት ሰባት ድምጽ ጋዜጣ የኤዲቶሪያል ቦርድ አባላት**
ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ፣አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ፣አቶ መሰፍን አማን፣አቶ ቸኮል ጌታሁን፣ሁሉም የቅንጅት ለአንድነትና ዴ ሞክራሲ ፓርቲ የላእላይ ምክር ቤት አባላት የነበሩ።

## ከገጽ 1 የዞረ የመለስን ግፈኛ አገዛዝ

"በሃገራችን ህግና ህገ መንግስት ተሸረው፣ የነበረችውም የህጋዊነት ጭላንጭል ተዳፍና የሰፈነው አገዛዝ ፍጹማዊ የግለሰቦች አምባገነናዊ አገዛዝ ነው። ይህ አገዛዝ በስልጣን ለመቆየት የሚተማመነው በዴሞክራሲዊ ምርጫ በመጣ ህዝባዊ ውክልና ወይም በህግና በህገመንግስት ላይ ሳይሆን በመቀጥቀጥ በመግደልና በማፈን ጉልበቱ ብቻ ነው። የሚተማመነው የሰራዊቱንና የፖሊስ አባላትን፣ እንዲሁም ህዝቡን ለማፈን ከፍተኛ የህዝብ ሃብት በማባከን ባደራጀው የአፈናና የስላለ ቡድን ነው። ይህንን አፋኝና ወንጀለኛ ቡድን ከሃገራችን ላይ ሳንነቅል ዴሞክራሲያዊ ስርአት መገንባት፣ ነጻነት መጎናጸፍ አይቻልም። ትግላችን በቅድሚያ መሆን የሚገባው ይህንን አፋኝ አገዛዝ፣ ያዋጣል ብለን ባሰብነው የትግል ስልት፣ ያዋጣል ብለን ባሰብነው ግዜ፣ ያዋጣናል ብለው በወሰነው አደረጃጀትና ያዋጣል ብለን ባሰብነው ህብረት ታግለን መጣል ነው።" የሚሉ ተቃዋሚ ሃይሎች እፍረት የሚባል ነገር ባለዘራባቸው የገኘው አካላት፣ የሃገር ክህደት፣ የአሸባሪነት ክስ እየተመሰረተባቸው ነው።

አጠቃላዩ ውግዘት፣ "የመለስ አገዛዝ በሃገሪቱ የሚኖረው ብቸኛ ፓርቲ የአገዛዙ የፖለቲካ ፓርቲ ብቻ ነው የሚል አዋጅ ማውጣት የቀረው አፋኝ ስርአት ነው" ከሚለው ከግንቦት7 ንቅናቄ አንስቶ "የሰላማዊና የህጋዊ መድረኩ ጠቧል መፈናፈኛም የለውም ግን በእዚሁም ሁኔታ ትግላችንን እንቀጥላለን" የሚሉትንም ቅን ግለሰቦችንና ድርጅቶችንም ይጨምራል።

ሰሞኑን አገዛዙ በቴሌቪዝን፣ በሬድዮ በድረ-ገጹ የሚወተውተው፣ በየሃገሩ በመደባቸው አምባሳደሮቹና በሃገራችን በተመደቡ የውጭ ሃገር አምባሳደሮች ወዳጆቹ በኩል ሊነግረን የሚፈልገው ሰላማዊና ህጋዊ የፖለቲካ መድረክ ያልተዘጋ መሆኑን ነው። አሁንም ህጋዊ በሆነ መንገድ ህገ መንግስቱን አክብረው ለሚታገሉ መንገዱ ክፍት እንደሆነ፣ ይህ እድል ለመኖሩ ደግሞ መድረኮች እየቆሙ፣ የፖለቲካ ስብሰባዎች እየተደረጉ፣ ጋዜጦች እየተጻፉ መሆናቸውን በማስረጃነት እያቀረበ ነው።

ጥያቄው፣ ለምንድን ነው የመለስ አገዛዝ ትኩረት ወደእዚህ አቅጣጫ የዞረው? ለምንድነው ወኪሎቹን በሙሉ በማንቀሳቀስ ግንቦት7 ንቅናቄ የሚለው አፋኝ ሁኔታ በኢትዮጵያ ውስጥ የለም የሚል የመከላከል ዘመቻ ማካሄድ ያስፈለገው? መለስ እንደ ጦር የሚፈራውንና እንደሬት የሚመረውን ስዬ አብርሃን በነጻነት መድርክ እየመሰረተ ነው ብሎ በማስረጃነት በቴሌቪዝን ያቀረበው። ወያኔ ኢህአዴግ ቢሳካለት ለእርድ ሊያቀርባቸው የሚመኛቸውን ግለሰቦች በድረ-ገጹ ማሞካሸት ያስፈለገው ለምንድነው? በተቃዋሚ መሃከል ልዩነት በመፍጠር እነዚህኞዎቹ ሰላማዊና ህጋዊ ትግል ለማድረግ የሚፈልጉ፣ የዴሞክራሲ ግንባታ ችግሩ የገባቸው አርቆ አሳቢዎች ናቸው፣ እነዚህኞቹ የስልጣን ፈላጊዎች፣ በህዝብ ላይ ፍጅትና እልቂት እንዲፈጠር የሚፈልጉ የጥፋት ሃይሎች ናቸው የሚል ማብራሪያ መስጠት የፈለገው? እውን እንደ መለስ የመሰለው ነፍሰ ገዳይ ከእዚህ ቀደም እራሱ ከቀጠፈው ነፍስ በተጨማሪ ሌላ ነፍስ እንዳይቀጠፍ ስለሚፈልግ? እስካሁን በዘረፋ ካካበተው፣ እስካሁን የአፈና ስርአቱን በመገንባት ካወደመው የሃገርና የወገን ሃብት ተጨማሪ ሳንቲም እንዳይባከን ስለሚመኝ ነው? ለምንድነው መግለጫውን ትቶ፣ ሰላማዊና ህጋዊ ትግል ማድረግ የሚቻልበት ሁኔታ አለ ማለቱን ትቶ፣ እንደልማዱ አመጽ አደራጅተው ሊታገሉኝ፣ ህጋዊ ከሆነው መንገድ ውጭ ለመሄድ የሚፈልጉ ሁሉ መንገዱን ጨርቅ ያድርግላቸው በሚል ንቀት ሊያልፈው ያልፈለገው? እንደዚህ ቀደሙ በተለመደው የእብሪት ቋንቋው ለምን በድንፋታ ብቻ መቀጠል አልመረጠም? መልሱ ግልጽ ነው።

ግንቦት7 የመለስ አገዛዝ የቆመባቸው የፕሮፓጋንዳና የድርጅት መሰረቶች ምን እንደሆኑ ጠንቅቀው በሚያውቁ አባላት የተሞላ ነው። መለስ አለኝ የሚለውን የፖለቲካ ጥበብና የማደራጀት አቅም ድንክዬ ማድርግ የሚችሉ፣ እሩቅ አልመው እሩቅ ማደር የማይሳናቸው፣ በአገዛዙ አስከፊነት ዙሪያ ሁሉንም የሃገሪቱን ህዝብ ማሰባሰብ የሚችሉ፣ የተለያዩ ችሎታና ሙያ ያለቸው አባላት ያሉት ድርጅት ነው። ግንቦት7 መለስ ዜናዊ በውሸት ወሬና ማስፈራሪያ እያወናበደ መገልገያ ሊያደርገው የሚፈልገውን ወገናችንን የትግራይ ህዝብ፣ የሰራዊቱንና የፖሊሱን አባላት፣ የመንግስት ሰራተኛውንና ዝቅተኛ ካድሬውን ለዴሞክራሲ፣ ለእኩልነት ለፍትህና ለአንድነት እንዲሁም ለዳር ድንበር መከበር ከኢትዮጵያውያን ወገኖቹ ጋር በአንድነት እንዲቆም ለማድረግ በሚችሉ አባላት የተሞላ ድርጅት ነው። ግንቦት7 ለመለስ ዜናዊ የስልጣን እድሜ መራዘም ምክንያት የፖለቲካ ድርጅቶች ህብረት መጥፋት መሆኑን አምሮ ከልቡ የተረዳ ድርጅት ነው። ይህን ህብረት ለመፍጠር፣ የተፈጠረውም ህብረት እንዳለፉት ትብብሮች በሰበብ አስባቡ እንዳይፈራርስ ማድረግ የሚያስችል የፖለቲካ ራእይ ያለው ድርጅት ነው። የግንቦት7 ንቅናቄ የመለስን አገዛዝ አረመኔያዊነትና ከሃዲነት በሚገባ ጠንቅቆ ባወቀ፣ ስለአገዛዙ ሌብነት መከራና ግፍ አምራችነት ተጨማሪ ማስረጃ በማይጠይቅ ህዝብ መሃልና ባበቃለት ሁኔታ ውስጥ የበቀለ ድርጅት ነው።ግንቦት7 ለነጻነታቸው ለክብራቸው፣ ለመብታቸው፣ ለሃገራቸውና ለህይወታቸው መሻሻል አማራጭ የሌለውን የመስዋእትነት ገፈት መጎንጨት የማያመልጡት እዳ መሆኑን የተረዱና ከተደበቱበት የነቁ ሚሊዮኖች፣ የድርጅት ያለህ በሚሉበት ሰአት የመጣ ድርጅት ነው።

የመለስ ዜናዊ አፈቀላጤ የሆኑ የመገናኛ አውታሮች፣ ይሄው ተቃዋሚዎች መድረክ እየፈጠሩ ነው። ተቃዋሚ ድርጅቶች ስብሳባ እያደረጉ ነው። ጋዜጦች የእነ እገሌን አክራሪ አመለካከት ሳይቀር እየዘገቡ ነው። ይሄው የታወቁ ግለሰቦች በሰላማዊና ህጋዊ መንገድ መታገል ይቻላል እያሉ ነው። የአሳባ ቁሊቱ የገበሬ መሃበር አባላት ባለሚሊዮኖች የሚያደርጋቸውን ወያኔ ኢህአዴግ መራሽ የኢኮኖሚ እድገት ለማሰናከል የተነሱትን የግንቦት7 ንቅናቄ አባላት እያወገዙ ማለት ወደ ቀረው ውትወታ የዶላቸው የግንቦት7 ንቅናቄን ምንነት በሚገባ በመረዳታቸው ነው። መለስንና አፈቀላጤዎቹ ከመዝገበ ቃላቶቻቸው ያጠፏቸውን፣ ትርጉማቸው ምን እንደሆኑ የማያውቋቸውን ሰላምና ህግ የሚሉ ክቡር ቃላት እያነሱ በኢትዮጵያ ህዝብ የፍትህና የነጻነት ጥማት ማላገጥ የጀመሩት እያስገመገመ ያለው ህዝባዊ ቁጣ አቁነጥጥነኗቸው ነው። በእዚህ ቁጣ አማካይነት የመለስን አገዛዝ የሃገራችን የመጨረሻው አምባገነናዊ አገዛዝ ለማድርግ እየተሰባሰቡ ያሉ የማይናቁ ሃይሎ መኖራቸውን በመረዳታቸው ነው።

ይህ የመለስ ዜናዊና የአፈቀላጤዎቹ የህግና የሰላም የማደናገሪያ፣ የማዘናጊያ ጨኸት ጊዜው ያለፈበት የተበላ ጨኸት ነው። የኢትዮጵያ ህዝብ በመለስና በበረከት ብልጠት አንዴ የተጭበረበረው በቅቶታል። በዴሞክራሲና በምርጫ ስም በፖለቲካ እምነቱ ተሰልሎ ከታወቀ በኋላ፣ሱሪውን አስወልቀው ብልቱን ከቀጠቀጡት ደሃ ገበሬ፣ ከተገደለው፣ ከታሰረው፣ ከተፈናቀለው፣ ከተሰደደው የእለት ጉሩሱን እንዲያጣ ከተደረገው ወገኑ በቂ ልምድ ቀስሟል። በነጻነትና በዴሞክራሲ ስም እየማሉ የኢትዮጵያ ህዝብ ለዴሞክራሲ በመቆሙ ብቻ ደሙ እንደጎርፍ ሲፈስ ከገዳዮቹ ጋር ያሴሩበትን የውጭ ሃገር መንግስታት ቃል አክብሮ እንደገና እንደከብት እራሱን ለእርድ አያቀርብም። መብት፣ ነጻነት፣ በህግ ፊት በእኩልነት መዳኘት፣ የመለስ ችሮታ የበረከት ገጸ- በረከት ሳይሆን፣ የሰውነትና የዜግነት መሰረታዊ መገለጫዎች መሆናቸውን ጠንቅቆ ያውቃል። ከእዚህ በኋላ፣ መውጫ መሄጃ አጥተው እባክህ ማረን፣ የማሪያም መንገድ ስጠን ብለው የሚለምኑት በረከትና መለስ እንጂ ይህ በእነዚህ እብሪተኛ ገዥዎች የዜግነት መብቱ ተገፎ የተዋረደ፣ አምኗቸው የተከዳ፣ በሃገሩ ላይ ወንጀል የተፈጸመበት ህዝብ ላይሆን ቃል ገብቷል። ግፉና ግብሩ የበዛበት የኢትዮጵያ ህዝብ ይህ ተግባር በቀቢጸ-ተስፋና በህልመኛነት የሚከናወን እንዳልሆነ ያውቃል። ቀበቶን፣ መቀነትንና ትጥቅን ጠበቅ፣ ሃሞትን ኮስተር በማድረግ ብቻ የሚሳካ ለመሆኑ ብዥታ የለውም።

ከገጽ 2 የዞረ **ኢ.ህአዴግ የዘረፈው ብር እየተድበሰበሰ ነው**

የመለስ አገዛዝ ለህሊናቸውና ለሙያቸው ቀናኢ የሆኑ ግለሰቦች በአገዛዙ ላይ የሚያቀርቡዋቸውን በጥናትና በመረጃ የተደገፉ የወንጀል ማስረጃዎች ማጣጣል ልማዱ መሆኑ ይታወቃል። ይህን ጉዳይ የቅርብ ግዜ ትውስታው የሆነው ሃገሬ "አሁን የቆመው ኮሚሽን ከእዚህ ቀደም በግንቦት 97 ምርጫ ወያኔ ኢ.ህአዴግ የፈጸመውን የግድያ ወንጀል ለማጣራት ተቋዋቁሞ የነበረውን ኮሚሽን ያቀረበውን ሃቀኛ ሪፖርት ለወያኔ በሚስማማ መንገድ ቀይሮ ለማቅረብ የተቁዋቁዋመውን በገዥው ስርአት ካድሬዎች የተሞላውን ተለጣፊ ኮሚሽን እንድናስታውስ ያደርገናል" እያለ ነው፡፡

በመሆኑም ሪፖርቱ በቀረበበት ዕለት "በአሰራራችን መሰረት በበጀት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ይታያል" ያሉት አቶ ሽፈራው፤ በቀጣዩ ቀን ቃላቸውን በማጠፍ ፡-"መታየት ያለበት በገለልተኛ ኮሚቴ ነው" በማለት የጌታቸውን የመለስን ሀሳብ አስተጋብተዋል፡፡

ምክትል ዋና ኦዲተሩ ማንንም ሳይፈሩ ያቀረቡት ሙያዊ ሪፖርት አንዳችም ስህተት እንደሌለበት በበርካታ የኢኮኖሚ ባለሙያዎች እየተመሰከረ ያለ ቢሆንም፣ ሲሳሳቱም ጭምር ጭብጨባ እንጅ ተግሳፅ ያልለመዱት ኢ.ህአዴጋውያን፣ በምክትል ዋና ኦዲተሩ በአቶ አሰፋ ላይ ቁጣቸውን ሲገልፁ ሰንብተዋል።

በተለየ መልኩ አቶ መለስ፣ የብሄራዊ ባንክ ገዥ አቶ ተክለወልድ አጥናፉ እና የገንዘብ ሚኒስትሩ አቶ ሶፊያን አህመድ ዋና ኦዲተሩን ሲወርፏቸው ሰንብተዋል።

አቶ መለስ፤ በመንግሰታቸው አሰራር ሳይሆን በራሳቸው ፈቃድ ያቋቋሙት ኮሚቴ ግራ ያጋባቸው አንድ የተቃዋሚ ፓርቲ አባል "የማጣራት ጥያቄ ያቀረበው ኢ.ህአዴግ፣ ከተፈቀደለት በጀት በላይ የተጠቀመው ኢ.ህአዴግ፣ ገለልተኛ ኮሚቴ መልምሎ ያቀረበው ኢ.ህአዴግ" ሲሉ ተደምጠዋል።

በጉዳዩ ዙሪያ አስተያየታቸውን እንዲሰጡን የጠየቅናቸው የአዲስ አበባ ነዋሪዎች፤ "የአገር ሀብት በአንድ ፓርቲ መዘረፍ የጀመረው ኢ.ህአዴግ ገና ስልጣን ላይ ሲወጣ ጀምሮ መሆኑን በማስታወስ፤ 'አሁንም በረሀብና በኑሮ ውድነት እየተሰቃየን ያለንበት ምክንያት አልጠፋንም" ብለዋል።

የሞተ ለማኝ ተፈልጎ ፤ ምናልባትም ተገድሎ ነው ፤ ቴዲን መክሰሻ ምክንያት የተፈጠረው ። ሃገሬውን «ወዮልህ!» ለማለት ። እንኩዋንስ «ራብኝ ነፃነት ጠማኝ ብለህ ልትጠይቅ ፤ ብታንጎራጉር እንኩዋ ፤ ውርድ ከራስህ ነው ተጠንቀቅ!» ለማለት::

በሽብር ለመግዛት:: የቴዲ እስራት የሥርአቱን ለከት የለሽ ጥጋብና ብልግና የሚያንፀባርቅ መስተዋታችን ነው ።

ቴዲ የኢትዮጵያ ህዝብ ሰቆቃ የወለደው የህዝብ ድምፅ ነው ። በአንደዚህ አይነት ወከባና ድቀት ወቅት ነው ቴዲዎች የሚወለዱት:: ከ150 አመታት በፊት መይሳው ቴዎድሮስ የተነሳው በመሳፍንት እዕብሪት ተዳክማና ኅብጣ የነበረችውን ኢትዮጵያችንን ትንሳኤ ለማምጣት ነበር:: በሳተ ተወልዶ በአረር ያለቀ የጀግና ህይወት ነበር ። ኢትዮጵያን ግን ከጅቡ መንጋጋ፤ መንጥቆ አወጣት:: የዘመናችን ቴዲም ነብስ የዘራው የወያኔ መሳፍንት መሃል ሃገሩን ይዘው፤ «ፀጥ ለጥ ብላችሁ ከልተገዛችሁ፤ አማራና ኦሮሞውን አጫርሰን እናንተ ስትባሉ እኛ ትግራይን በውድም ሆነ ሆነ በግድ እንገነጥላለን» ብለው በሚያስፈራሩበት አስከፊ ዘመን ነው:: ለወቅቱ የሚመጥን የሠላምና መቻቻል ጣዕመ ዜማዎችን በህሊናው ሃይል አምጦና ወልዶ እንካችሁ ያለን ጀግና ነው:: ለዚህ ህዝባዊና ሃገራዊ ግልጋሎቱ ደግሞ በወያኔ ሽብርተኞች ሰለባ መደረጉ የግድ ነው:: ነፃነት ውድ ዋጋ እንዳለው ዛሬ ቴዲ የሚገኝበት የቃሊቲ እስር ምስክር ነው:: በእብሪት የታጀለው ወያኔ-ኢህአዴግ ያልገባው ነገር ግን፤ ይህ ብልግና ሺህ ቴዲዎችን አየቀፈቀፈ መሆኑን ነው ።

አርብ ሐምሌ 4 ቀን የቴዲ ዕለተ ልደት ነበር ። 32 አመት ሆነው «ቅማል እየበላው» በእስር ቤት ነው ያከበረው ። መቀጣጫ ሆኖአል ተብሎ ሲታመን፤ ያው በተለመደ ስታሊናዊ ቅሌታቸው በመጨረሻ «ይቅርታ ጠይቆና ፈርሞ» መለቀቁን ይነግሩን ይሆናል:: ወደፊት ከመከሰስ የሚያድናቸው የህግ ሽፋን ያገኙ መስሎአቸው ነው የሃገር አዛውንቱን ሁሉ «ጥፋተኛ ነኝ ይቅር በሉኝ» ሰነድ የሚያስፈርሙት ። ያልገባቸው ነገር ግን በዚህ ተግባር የገነነበት መምህራቸው ጆሴፍ ስታሊንም ቢሆን ከህጋዊ ድንጋጌ በላይ ከትውልድ ወደ ትውልድ በሚወረስ የታሪ ክ ሚዛን ላይ ነብሰ-በላና ከይሲ ከመሆን እንዳላዳነው ነው ።

ከገጽ 1 የዞረ **የመለስ አገዛዝ ጸረ ኢትዮጵያዊነት መገለጫው**

ፍርድ ቤቱንም ሆነ የሚመለከታቸውን የመንግሥት አካላት የምጠይቀው ጉዳዩን በሚገባ ተረድተው በነፃ እንዲያሰናብቱኝ ነው።» ቴዲ አፍሮ

ካልጠፋ ርዕስ፣ አሁን በአንድ አዝማሪ መታሰር ላይ ምን አደከማችሁ የምትሉ ትኖሩ ይሆናል ። አዎን ቴዲ አዝማሪ ነው ። ቴዲ ወጣት ድምፃዊ ነው ። ቴዲ ሙዚቃ ደራሲና አቀናባሪ ነው:: ቅኔ ዘራፊ ነው ቴዲ የኢትዮጵያ ልሳን ነው ። ቴዲ የኢትዮጵያ ተ ስፋ ነው ።

የመቻቻል ትናጋችን ፤ የሠላም አርበኛችን ነው ። የአንድነታችን ጠበቃ ፤ የህብረታችን መንፈስ ነው ። በዚህም ሁሉ ምክንያት ነው ወህኒ የተወረወረው:: የኢትዮጵያ ህዝብ ናፍቆት የሆኑትን የነፃነትና መብትን ቀንዲል ያበራ ትሁት ሃገር ወዳድ በመሆኑ ነው ቴዲ በጨካኞች እጅ የሚሰቃየው:: አልሰደድ ብሎ ለእመ-ሃገሩ ስለሚያነባ ነው፣ ለሰላሳ ሽልንግ ወገን አልክድ፣ ለስልጣን አልሰግድ፣ ለጠመንጃ አልርድ ብሎ ነው የባለጌዎችን ጥላቻ ያተረፈው::

## ላለንበት ሁኔታ ከሚሰሩ ጥቅሶች፤ ከግንቦት7 አመራር አባላት የቀድሞ ጽሁፎች የተወሰደ፤

*"ድህነታችንን እና ኋላቀርነታችንን እያመላከቱ፣ ጥራቱ ከፍተኛ የሆነ ዴሞክራሲያዊ ስርአት እና ድርጅት ለመገንባት የምናደርገውን ትግል እንደማይሰካ፣ የመብት፣ የነጻነት የፍትህ እና የእኩልነት ፍርፋሪዎች እየለቀምን ብቻ በጸጋ እንድንኖር የስነልቦና ጫና ሲያደርሱብን የኖሩትን ገዥዎቻችን እና የውጭ ተባባሪዎቻቸውን አናደምጣችሁም ማለት አለብን:: የሰው ልጆች በፖለቲካ ራእይ እና ጽናት ብቻ ብዙ ፈታኝ የሆኑ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ፈተናዎች ማለፋቸውን በማመላከት፣ እኛም በሰውነታችን እና በኢትዮጵያዊ ዜግነታችን ከሚሰማን ክብር እና ኩራት ተነስተን እንደሌሎች የሰው ልጆች የገጠሙንን ፈተናዎች የማለፍ አቅም እንዳለን ለራሳችን እርግጠኞች መሆን ይኖርብናል::"*

ግንቦት 1997 ስለቅንጅት ውህደት ለመወያያ ከቀረበው ሰነድ